


MCPS MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

# ቅድመ ሙአለ ህፃናት/ሄድ ስታርት የተማሪ ምዝገባ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)በካውንቲው ጠቅላላ በገቢ-ሁኔታ ብቁ ለሚሆኑ ቤተሰቦች የቅድመ ሙዓለ ሕጻናት እና ሄድስታርት/prekindergarten and Head Start ፕሮግራሞችን በነፃ ይሰጣል። እነዚህ ፕሮግራሞች ልጆች ለሙአለ ህፃናት ዝግጁ ለመሆን የሚያስፈልጓቸውን ክሂሎቶችና እውቀት ይሰጣሉ።

የመመዝገቢያ ቦታ፡-

Rocking Horse Road Center
4910 Macon Road
Rockville, Maryland 20852
ሰኞ–አርብ 9:00 a.m.–4:00 p.m.
ያለቀጠሮ መግባት ይቻላል።
አስፈላጊ ከሆነ ቀጠሮ ለመያዝ ይቻላል።

## የ4 ዓመት ልጅ አለዎት?

**አዎን ከሆነ፤ እንግዲያዉስ ቤተሰብዎ በ MCPS ለነፃ የቅድመ ሙአለ ህፃናት ወይም የሄድ ስታርት ፕሮግራሞች ብቁ ሊሆን ይችላል።**

## የማስመዝገብ ሂደቱን ለመጀመር በ 240-740-4530 ይደዉሉ

### ደረጃ 1

**መግቢያ**

- የገቢ ማስረጃዎችን ማሟላትዎን ይወቁ/ይጠይቁ

240-740-4530 ይደውሉ

ሲያመለክቱ ሰራተኛዉ(ዋ)፡ -

- የተማሪንና የወላጅን ማንነት ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች
- የካውንቲ ነዋሪነትን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች
- የቤተሰብ ገቢን ያጣራል/ታጣራለች

### ደረጃ 2

**የአካል ምርመራ እና የክትባት መስፈርቶች**

- የጤንነት መረጃዎችን ይቀበላል/ትቀበላለች
- ለሁሉም ተማሪዎች ፈቃድ ካለው/ካላት የጤና ባለሙያ የአካል ምርመራ እና የተሟላ የመጀመሪያ ደረጃ ክትባቶች ማስረጃ አስፈላጊ ነው።

### ደረጃ 3

**የቤት ጉብኝት ወይም የመምህር/አስተማሪ ስብሰባ**

- የተሟላ/የተፈረመበት የጤንነት ማስረጃ አቅርብ/ቢ
- መምህር/አስተማሪ ስለ ትምህርት ክፍለ ጊዜዎችና አውቶብስ መጓጓዣ መረጃ ይሰጣል/ትሰጣለች፡፡

### ደረጃ 4

**ት/ቤት መገኘት**

- ማጓጓዣ አውቶቡስ ይቀርባል
- ከሰኞ እስከ ዓርብ ተማሪ በየቀኑ ትምህርት ይከታተላል/ትከታተላለች።

ይቀጥላል

# የምዝገባ ማስረጃዎችና በብዛት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሰነዶች

## የተማሪ እድሜ

### ለት/ቤት ብቁ ለመሆን፡-

- ተማሪዎች ሴፐቴምበር 1 ድረስ 4 ዓመት መድረስ አለባቸው።

### ምሳሌዎች

- የልደት ምስክር ወረቀት
- ፓስፖርት/ቪዛ
- የሃኪም ምስክር ወረቀት
- የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን የምስክር ወረቀት
- የሆስፒታል የምስክር ወረቀት/ሰርትፊኬት
- የወላጅ በህግ የተመዘገበ ቃለ-መሃላ (የተወለደ(ች)በትን ቀን ትክክለኛነት በማረጋገጥ በህጋዊ ቃል ተቀባይ የተመሰከረ ቃል)
- የልደት ምዝገባ
- ሌላ ህጋዊ ወይም በህጋዊ ቃል ተቀባይ የተመሰከረ የማንነት ማረጋገጫ

## ተማሪው(ዋ)ን አስመዝጋቢ ሰው መለያ እና ከተማሪው(ዋ) ጋር ያላቸው ዝምድና

- መታወቂያ እና
- ከተማሪ ጋር ስላለ ዝምድና ማስረጃ
- ሌሎች ጉዳዮች፣ ተገቢውን ቅጽ እና የሚያስፈልገውን ሰነድ ለመወሰን ከሰራተኞች/ስታፍ ጋር አብረው ይስሩ

### ምሳሌዎች

#### ፎተግራፍ ያለበት የወላጅ/ሞግዚት መታወቂያ ማረጋገጫ ምሣሌዎች፡-

- የመንጃ ፈቃድ
- ፓስፖርት
- የሞተር ተሽከርካሪ አስተዳደር (MVA) የመታወቂያ ካርድ
- ሌላ ህጋዊነት ያለው መታወቂያ

#### ከተማሪው(ዋ) ጋር ወላጅ/አሳዳጊ ስላላቸው ዝምድና-ግንኙነት ማረጋገጫ ምሳሌዎች፡-

- ስለ ወላጆች የሚገልጽ የተማሪ የልደት ሠርተፊኬት
- የፍርድ ቤት ትእዛዝ
- የመለያየት ስምምነት ወይም የፍቺ ድንጋጌ
- ሌላ ህጋዊ የሆነ መታወቂያ

## በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪነት

### የመኖርያ ቤት ባለቤት

- ወቅታዊ የንብረት ግብር ማስከፈያ-ቢል ቅጂ ማቅረብ

### ተከራይ

- ወቅታዊ የሊዝ ማስረጃ ቅጅ/ኮፒ ይስጡ (የመጀመሪያው ሊዝ ጊዜ አልፎበት ከሆነ፣ የሊዙን ቅጂ እና የፍጆታ አገልግሎት ክፍያ ቢል)

### የደባል ቤት

- ከቤት ባለቤት ወይም ከተከራይ ዶኩመንት/ሠነድ እና የተሞላ የ MCPS Form 335-74 ቅጽ አቅርብ(ቢ) ስለቤት ደባልነት መግለጫ

### ቤት-የለሽ

- የ MCPS Homeless Liaison በስልክ ቁጥር፡- 240-740-4511 ማግኘት ይችላሉ

### ምሳሌዎች

- ደጋፊ ማስረጃዎቹ በ MCPS ቅጽ 335-74 አድራሻ ላይ በተገለጸው ወላጅ/ሞግዚት ስም የተመዘገቡ መሆን አለባቸው ቤት በደባልነት የመጋራት መግለጫ ቅጽ/Shared Housing Disclosure Form የላኪውን ድርጅት ስም፣ እና እስከዛሬዉ እለት 90 ቀን ያላለፈበት ቀን ይጨምሩ።
- ስለ አድራሻ የሚገልጹ ተቀባይነት የሚኖራቸው የልዉዉጥ ሠነዶች ከሚከተሉት ዓይነት ድርጅቶች መሆን አለበት፡-
- የገንዘብ ተቋማት (ማለት፡- ባንኮች፣ የመድን/የኢንሹራንስ ድርጅቶች፣ ወ.ዘ.ተ)
- የፍጆታ/ዩቲሊቲ ኩባንያዎች (ማለት፡- የስልክ፣ የውኃ፣ የማብራት-ኃይል፣ ወ.ዘ.ተ)
- መንግስታዊ (ማለት፡- ፌደራል፣ ስቴት፣ የአካባቢ)
- ህክምና
- የኃይማኖት ተቋማት
- አትራፊ ያልሆኑ/የማህበረሰብ ድርጅቶች

## የቤተሰብ ገቢ ማረጋገጫ

- የሁሉም አዋቂ የቤተሰብ አባል ወቅታዊ የገቢ ማስረጃ መቅረብ አለበት

### ምሳሌዎች

- የመጨረሻዎቹ የሦስት ክፍያዎች ማስረጃ
- የወቅቱ የገቢ ታክስ ቅጽ/ፎርም
- የቅጥር ደብዳቤ
- የሥራ አጥ ጥቅማጥቅሞች
- በህግ የተረጋገጠ የገንዘብ ድጋፍ ደብዳቤ
- የ Temporary Cash Assistance (ጊዜያዊ የጥሬ ገንዘብ ድጎማ (TCA) ክፍያዎች